AMHARIC

# የጥላቻ ነክ ወንጀል




WELSH REFUGEE COUNCIL
CYNGOR FFOADURIAID CYMRU
www.wrc.wales

# የጥላቻ ነክ ወንጀል

## አንድ ነገር ማድረግ ይችላሉ!

ሰላም፣ ወደ ዌልስ እንኳን ደሕና መጡ! ወደ ዌልስ አዲስ የሚመጡ ሰዎች ማሕበረሰባችንን ሊያበለጽጉ የሚችሉ አስደናቂ ባሕሎችን፣ ተሰጥኦዎችና ችሎታዎችን ይዘው እንደሚመጡ በማወቃችን ደስተኞች ነን። ስለዚህ፣ ሕይወት በዌልስ ውስጥ ምን ይመስላል?



ዌልስ ውብ ሐገር ስትሆን አብዛኞቹ ሰዎችም በጣም ተግባቢ ቢሆኑም አንዳንዶቹ ግን እንደዚህ



አሃ... ለምን እንደዛ አሉ? የተፈጠረ ነገር አለ?

ከተወሰነ ጊዜ በፊት በአውቶብስ በመጓዝ ላይ እያለሁ አንድ ሰው ጸያፍ ቃላትን ይሰነዝርብኝ ጀመረ፣ ወደ ሃገሬ ተመልሼ እንድሄድም ይናገር ነበር። እንዲያቆም ስጠይቀው የሆነ ነገር ወረወረብኝ። የወረወረብኝ ነገር ፍራፍሬ መሰለኝ። በወቅቱ በጣም ሃፍረትና ፍርሃት ስለተሰማኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር።

እንዴት ያስጠላል፣ መጥፎ ስሜት ስለተሰማዎት አልገረመኝም። ግን የእርስዎ ጥፋት እንዳልሆነ ያውቃሉ አይደል? **ይህ ክስተት ጥላቻ የፈጠረው ነው።** ስለጉዳዩ ለፖሊስ ማሳወቅ ይችላሉ። እነርሱ ድርጊቱ ጥላቻ ነክ ወንጀል ነው ብለው ካሰቡ እርምጃ መውሰድ ይችላሉ። ጉዳዩን አጻምጠው ድጋፍ በመስጠት ድርጊቱ **ጥላቻ ነክ ወንጀል** ተብሎ ሊመደብ እንደሚችል ይወስናሉ። ጥላቻ ነክ ወንጀል ነው ብለው ባይመድቡት እንኳን እርስዎ ሪፖርት በማድረግ ድጋፍ ማግኘት ስለሚችሉ እርስዎን ያግዝዎታል። ሁኔታውን ለብቻዎ መጋፈጥ አይጠበቅብዎትም!



ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ? **ጥላቻ ነክ ወንጀል ምንድን ነው?**



**ጥላቻ ነክ ወንጀል ወይም ጥላቻ ነክ ክስተት ማለት** በዘርዎ፣ በኃይማኖትዎ፣ በእምነትዎ፣ በአካል ጉዳትዎ፣ ሁለት-ጾታዊ ማንነትዎ ወይም ጾታዊ ዝንባሌዎ ምክንያት **የሚፈጸሙብዎ የጥላቻ ድርጊቶች ናቸው።** ጥላቻው በእርስዎ ላይ ያነጣጠረ ሆነ በሌላ ሰው ላይ ሲፈጸም ካዩ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። የቤተሰብዎ አባላት፣ ጓደኞችዎ፣ ገና የተዋወቁት ሰው ወይም የማያውቁት ሰው ሊሆን ይችላሉ።

ጥላቻ ነክ ወንጀል በየትኛውም ቦታ ሊፈጸም ይችላል፤ በቤትዎ፣ በአውቶብስ ውስጥ፣ በፓርክ ወይም በት/ቤት ወይም በዩኒቨርሲቲ ሊከሰት ይችላል።

## እውነታ፡

ጥላቻ ነክ ወንጀል በማንነትዎ ወይም በሚወክሉት ነገር ምክንያት የሚፈጸምብዎ ሕገ-ወጥ የጥላቻ ድርጊት ነው።



## ግለሰቡ ድርጊቱን የፈጸመው በትክክል ማሰብ የማይችል ሰው ስለሆነ ቢሆንስ?

ስለ እርስዎ ግምት ወስዶ በዚህ ግምት ላይ ተመስርቶም ጥቃት ፈጽሞብዎታል። ይህ ደግሞ በዩኬ ውስጥ ተቀባይነት የለውም። **ይህን ማድረግም ሕገ-ወጥና ወንጀል ሊሆንም ይችላል!** በቤትዎ፣ በማሕበረሰብዎ ውስጥና በሕዝባዊ ቦታዎች ላይ ደህንነት የመሰማት መብት አለዎ።

በሰዎች ላይ ሊፈጸሙ የሚችሉና ተቀባይነት የሌላቸው በርካታ ነገሮች አሉ፤ እነዚህ ነገሮች ወደ ጥላቻ ነክ ክስተት የሚቀየሩት ደግሞ የድርጊቱ ምክንያት አንድ ሰው በእርስዎ ላይ የራሱን ግምት በመውሰዱ ከሆነ ነው።

- ከእነዚህ ድርጊቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡
- መገፍተር፣ መዋከብ ወይም የዛቻ ሰለባ መሆን፣
- የሆነ ነገር ሲወረወርብዎት ወይም በደብዳቤ መቀበያ ሳጥንዎ በኩል መጥፎ ነገር ሲጻፍብዎት፣
- አንድ ሰው በሚያስፈራራ ሁኔታ ወደእርስዎ አቅጣጫ ሲቀርብ፣
- በቃላት የማይገለጹ አስነዋሪ ምልክቶች ወይም በድምጽዎ የማሾፍ ድርጊት ሲፈጸም፣
- ምራቅ ሲተፋብዎት፣ ሲደበደቡ ወይም ሲረገጡ፣
- በጸያፍ ስም ሲጠሩ፣ ሲሾፍብዎት ወይም አስቀያሚ ቀልዶች ስለእርስዎ ሲቀለዱ፣
- ንብረትዎ ጉዳት ሲደርስበት ወይም ሲሰረቅ፣
- በኀረቤት ጥቃት ሲደርስዎብዎት፣
- ከኀረቤቶች ጋር የእሳት ቃጠሎ ጥቃት ወይም አለመግባባት ሲከሰት፣ እና
- በአካል ጉዳትዎ፣ በዘርዎ፣ ኃይማኖትዎ፣ ፆታዊ ዝንባሌዎ ወይም ባለ ሁለት ፆታ በመሆንዎ ምክንያት ሲቀለድብዎት።





## እሺ፣ ግን እንዴት ነው ሪፖርት የማደርገው?

ጉዳዩ አጣዳፊ ሲሆን ወደ **999** ደውለው ሪፖርት ማድረግ የሚችሉ ሲሆን፡

- ክስተቱ አሁን ከተፈጸመና እርስዎም አስቸኳይ ድጋፍ የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣
- ጥቃት ፈጻሚው አሁንም በአቅራቢያዎ ካለ፣
- በእርስዎ ወይም በሌላ ሰው ሕይወት ላይ አደጋ እንደተጋረጠ ከተሰማዎ ወይም
- አካላዊ ጥቃት ከደረሰና እርስዎም ስጋት ከገባዎት ነው።

ወደ **101** መደወል ያለብዎ

- ሁኔታው የተከሰተው ከተወሰነ ጊዜ በፊት ከሆነና እርስዎ ሪፖርት ማድረግ ከፈለጉ፣
- ጥቃት የፈጸመብዎት ግለሰብ በአቅራቢያዎ ከሌለ፣
- አሁን በእርስዎም ሆነ በሌላ ሰው ላይ የተጋረጠ የአደጋ ስጋት ከሌለ፣ እና
- በእርስዎ ላይ አካላዊ ጥቃት ካልተፈጸመ ነው።

## ወደ 999 ወይም 101 ይደውሉ

"ጥላቻ ነክ ወንጀል ሪፖርት ለማድረግ እፈልጋለሁ" ማለትዎን አይርሱ

## ሪፖርት ካደረግሁ በኋላ ምን ይከሰታል?




ጥላቻ ነክ ወንጀልን ሪፖርት ሲያደርጉ፣ ፖሊስ የእርስዎን ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በሙሉ ይወስዳል። እርስዎ ለመነጋገር የሚፈልጉት በፖሊስ ጣቢያ ካልሆነ ወይም በስልክ ለማውራት ካልፈለጉ በስተቀር ፖሊሶች እርስዎን ለማግኘት የሚመጡ ሲሆን እርስዎን የሚመለከቱ መረጃዎችም በሚስጥር ይያዛሉ። ምን እንደተከሰተ ፖሊስ የእርስዎን ቃል በማድመጥ በምርመራው ሂደት ወቅት እንደ Victim Support ካሉ ሌሎች ድርጅቶች ድጋፍ እንዲያገኙ ያግዝዎታል፡ ፡ አስፈላጊ ከሆነም ፖሊስ ግለሰቡ እርስዎን ደግሞ እንዳያገኝ ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶችንም ሊፈልግ ይችላል። በሁሉም የዌልስ ፖሊስ ኃይል ውስጥ የጥላቻ ነክ ወንጀል ድጋፍ ሰጪ የተመደቡ መኮንኖች ያሉ ሲሆን እነርሱም እርስዎን ለማገዝና ለመደገፍ ይችላሉ።

ከግለሰቡ ጋር እንዲነጋገሩ፣ እንዲገናኙ ወይም ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖርዎ አይጠየቁም፤ ነገር ግን የሚከተሉትን እንዲፈጽሙ ሊጠየቁ ይችላሉ፡

- ቃል እንዲሰጡ፣
- በሞባይል ስልክ የተነሳ ፎቶ ወይም ሲሲቲቪ፣ የአካል ጉዳት ወይም ፎቶዎች የመሳሰሉ ማናቸውም ማስረጃዎችን እንዲሰጡ፣
- የተጠቂ ተጽእኖ መግለጫ እንዲሰጡ፤ በእርስዎ ላይ ስለተፈጸመው ድርጊት የሚሰማዎት ስሜትና በሕይወትዎ ላይ ስላስከተለው ተጽእኖ እና
- በ Victim Support ተወካይ እየታገዙ በፍ/ቤት ቀርበው ማስረጃ እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይችላሉ።



## ሪፖርት ማድረግ አስፈላጊነቱ ባይሰማኝስ? ምናልባት ሪፖርት ማድረጉ ሁኔታውን ቢያባብሰውስ?





ስለ ክስተቱ ከማንም ሰው ጋር ለመነጋገር ካልፈለጉ፣ በ Victim Support ድረ ገጽ ላይ **www.reporthate.victimsupport.org.uk/hate-crime/**ሪፖርት ማድረግ የሚችሉ ሲሆን ከዚህ ገጽ ላይ የሚፈልጉትን ቋንቋ መምረጥ፣ ቅጹን መሙላትና በቀጣዩ አድራሻ ኢሜይል መላክ **hate.crimewales@victimsupport.org.uk** ወይም ከክፍያ ነጻ በፖስታ ቤት በኩል ለሚከተለው መላክ ይችላሉ፡ ወይም በዚህ ቁጥር ይደውሉ፡ **03003031982**.
Free Post RTJR-RLRR-RCEJ, Victim Support, PO Box 1096, Cardiff, CF11 1TP

## ያስታውሱ፡

ጥላቻ ነክ ወንጀልን ሪፖርት ለማድረግ ከማንም ጋር መነጋገር አያስፈልግዎትም፤ ኦንላይን ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።



### እኔ ጥገኝነት ጠያቂ በመሆኔ በራሴ ላይ ትኩረት ለመሳብ ባልፈልግስ? ምንም ዓይነት ችግር ውስጥ መግባት አልፈልግም፤ እንደዚሁም የጥገኝነት ጥያቄዬ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ነገር አልፈልግም።

ጥላቻ ነክ ወንጀሎችና ክስተቶች የሚስተናገዱት በአካባቢዎ ባለ የፖሊስ አካል በመሆኑ በጥገኝነት መጠየቂያ ማመልከቻዎ ላይ ተጽእኖ አይኖረውም። አንድ ሰው በማንነትዎ ወይም እርሱ ስለእርስዎ ባለው አስተሳሰብ ምክንያት ሊጎዳዎ ከሞከረ፣ ጥፋቱ የእርስዎ አይደለም። የምርመራው ሒደት የጥገኝነት ማመልከቻ ቀጠሮዎችዎን እንዳያደናቅፍ ፖሊስ የሚተባበርዎ ሲሆን የጥላቻ ነክ ወንጀል ሪፖርትዎ ዝርዝርም በሆም ኦፊስ ለሚሰሩት የኬዝ ባለቤት ተላልፎ አይሰጥም።


በተጨማሪም፣ ጥላቻ ነክ ወንጀልን ሪፖርት ማድረግዎ የማረፊያ ወይም የቤት ድጋፍዎን የማይጎዳ ቢሆንም በጥላቻ ነክ ክስተቱ ምክንያት ደህንነቱ የተሻለ ማረፊያ ቦታ ከፈለጉ፣ በዚህ ረገድ ድጋፍ ይደረግልዎታል።



### ራሴ ሪፖርት ማድረግ ባልፈልግስ፣ ሌላ ሰው ሪፖርት ሊያደርግልኝ ይችላል?



አዎ፣ ለ Victim Support በስልክ ቁጥር 0300 303 1982 መደወል የሚችሉ ሲሆን እነርሱም እርስዎን ወክለው ሪፖርት ያደርጉታል። በተጨማሪም፣ በአካባቢዎ የሚገኝ ኤጀንሲ እርስዎን ወክሎ ሪፖርት እንዲያደርግልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ድጋፍ ሊያደርጉልዎ ከሚችሉ ድርጅቶች መካከል የ Welsh Refugee Council, Citizens Advice Bureau እና የ British Red Cross ይገኙበታል።



## ያስታውሱ፣

ጥላቻ ነክ ወንጀልን ሪፖርት ለማድረግ ከማንም ጋር መነጋገር አያስፈልግዎትም፤ ኦንላይን ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

## ጥቃት ያደረሰብኝን ግለሰብ በግልጽ ማስረዳት ባልችልም የጥላቻ ነክ ወንጀልን ሪፖርት ማድረግ እችላለሁ?



አዎ። አንድን ክስተት በተመለከተ የሚሰጡት ማንኛውም መረጃ ጠቃሚ ሊሆንና በአካባቢዎ በሚገኝ ሌላ ሰው ላይ ከተፈጸመ ተመሳሳይ ድርጊት ጋር ሊመሳሰል ይችላል። ፖሊስ ግለሰቡን ሊያውቀው የሚችል ሲሆን ከሞባይል ስልክ ወይም ከሲሲቲቪ ካሜራ ስለ ክስተቱ ማስረጃ ሊያገኝ ይችላል። ክስተቱ ይበልጥ እስከፊ ወደሆነ ጥላቻ ነክ ወንጀል እንዳያድግ ለመከላከልም ይችላሉ። **ስለዚህ እባክዎ ለሆነ ሰው ሪፖርት ያድርጉ።**



## ፖሊስ ድርጊቱ ጥላቻ ነክ ወንጀል ነው ብሎ ባያስብስ?



ክስተትዎ እንደ ጥላቻ ነክ ወንጀል ካልተቆጠረ፣ ፖሊስ ስለወሰደው እርምጃ መረጃ የሚሰጥዎ ሲሆን Victim Support ደግሞ እርስዎን ማገዙን ይቀጥላል።



## ክስተቱ ጥላቻ ነክ ወንጀል መሆኑን ማረጋገጥ አለብኝ?

የለም። በዘርዎ፣ በኃይማኖትዎ፣ በአካል ጉዳትዎ፣ በጾታዊ ዝንባሌዎ ወይም ጾታዊ ማንነትዎ ምክንያት የጥላቻ ሰለባ ሆኛለሁ ብለው ካሰቡ፣ ፖሊስ የተፈጸመውን ክስተት እንደ ጥላቻ ነክ ወንጀል መቁጠር አለበት። ምንም እንኳን የተፈጸመው ድርጊት በወንጀል የማያስጠይቅ ቢሆንም (በፖሊስ አጠራር የጥላቻ ክስተት ይባላል) ፖሊስ ጉዳዩን መርምሮ ድጋሚ እንዳይከሰት ለማድረግ የሚያስችል እርምጃ የሚወስድ ሲሆን እርስዎም ከጥላቻ ነክ ወንጀል ድጋፍ ሰጪ የተመደቡ መኮንን ድጋፍ ያገኛሉ።



## ያስታውሱ፡

ፖሊስ ስለ ሪፖርትዎ ማስረጃ ለማግኘት የሞባይል ስልክ ምስሎችን ወይም የመንገድ ላይ ካሜራ ቀጂዎችን ሊጠቀም ይችላል።

## ሪፖርት ማድረጉ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?



በርካታ ጥላቻ ነክ ወንጀሎች ሪፖርት ሳይደረጉ ይቀራሉ። ጥላቻ ነክ ወንጀል ሪፖርት ሲያደርጉ፣ በእርስዎ፣ በጓደኞችዎና በቤተሰብና ማሕበረሰብዎ ላይ ልዩነት ይፈጥራል። ድርጊቱ ሲፈጸም ሪፖርት በማድረግዎት፡

- በእርስዎ ወይም በሌላ ሰው ላይ ከመፈጸም ለማስቆም ማገዝ ይችላሉ፣
- ጥገኝነት ጠያቂዎችና ስደተኞች የሚያሳስባቸውን ጉዳይ ለማጉላት ማገዝ ይችላሉ።
- በአካባቢዎ ስለሚፈጸም ጥላቻ ተኮር ወንጀል መጠንና እንዴት መከላከል እንደሚቻል ፖሊስ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው ማገዝ ይችላሉ፤ እንደዚሁም
- ፖሊስ ለጥላቻ ነክ ወንጀሎች ምላሽ የሚሰጥበትን መንገድ እንዲያሻሽል ማገዝ ይችላሉ።

የግል መረጃዎን ለመስጠት ካልፈለጉ፣ ምን እንደተከሰተ ብቻ ይንገሯቸውና እርስዎ የሰጡትን መረጃ በመጠቀም በአካባቢዎ የሚፈጸሙ የጥላቻ ነክ ወንጀል ድርጊቶችን ለመከታተል፣ የማሕበረሰብዎን ደህንነት ይበልጥ ለማረጋገጥና ሰዎች በደረሰባቸው ነገር የሚሰማቸው የመገለልና የፍርሃት ስሜት እንዲቀንስ ለማድረግ ይችላሉ። ፖሊስም ሪፖርት የተደረጉለትን የጥላቻ ነክ ወንጀሎችን በሙሉ ይመዘግባል። የተፈጸመው ድርጊት ወደ ፍ/ቤት የማያመራ ቢሆንም እንኳን፣ ሁኔታዎች እንዳይባባሱ ለመከላከል ከእርስዎና ከሌሎች የጥላቻ ወንጀል ላይ ድጋፍ ሰጪ ኤጀንሲዎች ጋር አብረው መስራታቸውን ይቀጥላሉ።



## ፖሊስ የእኔን ሃሳብ ባያዳምጠኝስ?

አንድ ጓደኛዬ መንገድ ላይ ዕንቁላል በተወረወረበት ጊዜ ፖሊስ ቃል የተቀበለው ቢሆንም ሌላ ነገር ግን አላደረጉለትም።




የፖሊስ መኮንን ወይም የፖሊስ አባል የሆነ ሰው ሃሳቤን አላዳመጠኝም ወይም በአግባቡ አላስተናገደኝም ብለው ካሰቡ፣ **በጉዳዩ ላይ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።** በአካባቢዎ ወደሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ቅሬታዎን ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ጉዳይዎም ወደ Professional Standards Department እንዲተላለፍ መጠየቅ ይችላሉ። ሁሉም የፖሊስ መ/ቤቶች ይህን አገልግሎት ይሰጣሉ። በአካባቢዎ ላሉት የፓርላማ አባል ወይም የጉባዔ አባልም ማሳወቅ ይችላሉ፣ እርሳቸውም ቅሬታዎን እንዲያቀርቡ ሊያግዙዎት ይችላሉ፤ ወይም ለራስቻል ቅሬታ-ሰሚ ፓሊስ-ኮሚሽን (Independent Police Complaints Commission (IPCC)) በቀጣዩ ድረ ገጽ ማመልከት ይችላሉ፡ **www.ipcc.gov.uk** ። ጠበቃ ካለዎትም በጠበቃዎ በኩል ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። አካባቢዎን ወክለው የተመረጡ የፓርላማ አባልን ለማግኘት **https://members.parliament.uk/members/Commons** በመግባት ሊንኩ ላይ ክሊክ ያድርጉ። አካባቢዎን ወክለው የተመረጡ የጉባዔ አባልን ለማግኘት ወደ ቀጣዩ ድረ ገጽ ይግቡ፡ **www.senedd.assembly.wales/mgFindMember.aspx**

### አንዳንድ ድርጅቶች  እርስዎን ወክለው ጥላቻ ነክ ክስተቶችን ሪፖርት ሊያደርጉ ይችላሉ፡

- የብሪተን ቀይ መስቀል ድርጅት፡ 01633 245 774
- የዜጎች ኣማካሪ ቢሮ : 03444 772 020
- የተጎጂዎች ድጋፍ ሰጪ ቢሮ: 0300 303 1982
- የዌልስ ስደተኞች ምክር ቤት: 02920 489 800

## ያስታውሱ፡

የጥላቻ ወንጀሎችን ሲትዘግቡ፡ ለርስዎ፣ ለጓደኛዎ፣ እና ለማህበረሰብዎ፡ ሊዩነት ይፈጥራል።




# ምስጋና

ይህ ጥላቻ ነክ ወንጀልን የሚመለከት በራሪ ወረቀት በዌልስ ውስጥ የሚፈጸሙ ጥላቻ ነክ ወንጀሎችንና ክስተቶችን ለመረዳት፣ እንዴት ሪፖርት መደረግ እንዳለበት ለማወቅና እንዳይከሰት ለመከላከልም እንዴት ሪፖርት ማድረግ እንዳለብዎ ግንዛቤ እንዲኖርዎ ለማድረግ የተዘጋጀ መምሪያ ነው። የ Welsh Refugee Council ይህን መረጃ ከእርስዎ ጋር በመጋራቱ ደስተኛ ሲሆን በተለይ ደግሞ ይህን በራሪ ወራት ለማዘጋጀት ከእኛ ጋር አብረው የሰሩ ድርጅቶችን ለማመስገን ይወዳል።

VICTIM SUPPORT CYMRU | WALES

Ariennir gan Lywodraeth Cymru
Funded by Welsh Government